ነቢዩ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- ፀጉር የምትቀጥልን፣ የምታስቀጥልን፣ የምትነቅስንና የምታስነቅስን ረግመዋል።

ከዐብደላህ ቢን ዑመር ረዲየሏሁ ዐንሁማ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "ነቢዩ ሶለሏሁ
ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- ፀጉር የምትቀጥልን፣ የምታስቀጥልን፣ የምትነቅስንና
የምታስነቅስን ረግመዋል።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- አራት አካላቶች ላይ እርግማንንና ከአላህ እዝነት መራቅን ዱዓ አደረጉባቸው። የመጀመሪያው: የራሷን ወይም የሌላን ሰው ፀጉር በሌላ ፀጉር የምትቀጥል ናት። ሁለተኛው: ሌላ ሰው ፀጉሯን በሌላ ፀጉር እንዲቀጥልላት የምትጠይቅና የምታስቀጥል ናት። ሶስተኛው: ማማርና ውበትን በመፈለግ ፊትን ወይም እጅን ወይም ደረትን የመሰሉ የሰውነት አካላቶችን በመርፌ በመጠቅጠቅ ምልክቱ ሰማያዊ ወይም አረንጓዴ እስኪሆን ድረስ ኩልን ወይም የመሳሰሉትን ቦታው ላይ እየቀባች የምትነቅስ ናት። አራተኛ: ንቅሳት እንዲፈፀምባት የምትፈልግ ናት። እነዚህ ተግባራት ከትላልቅ ወንጀሎች መካከል የሚመደቡ ናቸው።

http://www.sunnah.global/hadeeth/am/show/58099